# ኢሕአፓ በሲያትል

በዋሽንግተን ስቴት በሲያትልና አካባቢዉ የሚገኙ የኢሕአፓ አባላተና ደጋፊዎች ያዘጋጁት የዉይይት ቀን ባለፈዉ ቅዳሜ ማርች 26/2011 በአሲምባ ሬስቶራንት አዳራሽ በሲያትልና አካባቢዉ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበትና በተሳተፉበት ሁኔታ ከተጠበቀዉ በላይ ስኬታማ በሆነ መንገድ ተከናዉኗል። የዝግጅቱ አላማ እናት ሀገራቸዉ ያለችበት ሁኔታ ከልብ ለሚያሳስባቸዉ፡ ለሚያስጨንቃቸዉና ላለፉት አስራዘጠኝና ሀያ ዓመታት አገራችንን ከወደቀችበት አዘቅት ለማዉጣት በተደረጉት የትግል እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተለያዩ መንገዶች አስተዋፅኦ ሲያደርጉ ለቆዩና በሲያትልና አካባቢዉ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ፤ ኢሕአፓ ባሁኑ ወቅት በሃገር ዉስጥና በዉጭ እያካሄደ ባለው እንቅስቃሴ ላይና በሃገራችንንና በዓለም አቀፍ ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ገለፃና ማብራሪያ ለመስጠትና ለመወያየት ነበር።

በዚህም መሰረት፤ ዉይይቱ የተጀመረዉ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ፋሲካ በለጠ በተንቀሳቃሽ የድምፅ ማጉያ መሳሪያ በተደገፈ የስልክ ግንኙነት አማካይነት ስለ ወቅቱ ሁኔታና ስለኢሕአፓ እንቅስቃሴ ባደረጉት ሰፊ ገለፃና ማብራሪያ ነበር። ከገለፃዉ በዉሓላም፡ ከዉይይቱ ተሳታፊዎች ለቀረቡ በርካታ ጥያቄዎችና ገንቢ አስተያቶች ፤ አጥጋቢ መልስና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

አቶ ፋሲካ በሰጡት ሰፊ ማብራሪያም፡ በመካከለኛዉ ምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ እየተካሄዱ ያሉትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች በሰፊዉ በመተንተንና በማስረዳት እንዲሁም እነዚህ እንቅስቃሴዎች በሐገራችን ላይ ስለሚኖራቸው ተፅእኖ ፤ ከአገራችን ሁኔታ ጋር ስለሚኖራቸው ተመሳሳይነትና ልዩነት በመተንተን ሰፊ ገለጻ አድርገዋል። በየትኛዉም ሃገር የሚነሱ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሕዝባዊ ብሶትና ቁጣ መግለጫ ሲሆኑ በቀነ ቀጠሮ፤ በዚህ ቀን፤ በዚህ ቦታ፤ በዚህ ሰዓት፤ በዚህ ወር ይነሳል ብሎ መገመት እንደማይቻልና፡፤ ምን ልዩ ሁኔታ የመጀመሪያዉን አቀጣጣይ ክብሪት ሊጭር እንደሚችልም መገመት እንደማይቻል ገልጸው፤ ነገር ግን ሕዝብ መብቱን ከተቀማ፤ ከተራበ፤ በገዛ ሃገሩ ላይ ባይተዋር ከሆነ፤ ሰብአዊ መብቱ ከተገፈፈና ባጠቃላይ፤ አፈናና አመቃን፤ የህዝብን መብት አፍኖ የመግዣያ ሀይልን መሠረት ያደረገ አምባገነን ሥርዓት ከሰፈነ፤ የህዝብ ብሶትና ቁጣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እተከማቸና እየ ጨመረ የሕዝብ ብሶትን የመጨረሻ ደረጃ ላይ ሊያደርስ እንደሚችልና ይህም ለሕዝብ አመጽ መከሰት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ባጠቃላይ መናገር ይቻላል ብለዋል።፤ በሕዝባዊ አመጽ ወቅት ሕዝቡ በትግሉ ዉስጥ ቁርጠኛነትንና አይበገሬነትን ካሳየ አምባገነኖች ባጭር ጊዜ ከሥልጣን ሊወገዱ መቻላቸዉን አስረግጦ መናገር እንደሚቻል አስምረዉበታል።

በመቀጠልም በመካከለኛዉ ምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ አገሮች የተነሳዉ ሕዝባዊ አመፅ/እንቅስቃሴ ለአገራችን አዲስ እንዳልሆነ፡ የየካቲት ሰድሳ ሰድስቱ ሕዝባዊ አብዮት ገና የተረሳ እንዳልሆነ፤ የህዝቡ ድል በወታደሮች ይነጠቅ እንጂ ከባድ ፈተናዎችን ተቋቁሞና ብዙ መስዋትነት ተከፍሎ ፤ የነበረዉን ስርዓት መገርሰስ እንደተቻለ፤ በወያኔም ጊዜ ቢሆን ግባቸዉን አይምቱ እንጅ ወጣቶች መስዋትነት የከፈሉበት በርካታ የተቃዉሞ እንቅስቃሴዎች እንደተደረጉ፤ በ1997 ዓ. ም የተካሄደዉ የተቃዉሞ እንቅስቃሴም በአጭር የተቀጨ የሕዝብ ብሶትና ቁጣ የወለደዉ እንቅስቃሴ እንደነበርና ከራሳችን የሕዝባዊ አመፅና ሁኔታ ብዙ መማር እንደምንችል አስረግጠዉ አስረድተዋል። አሁንም እንደገና ለዚህ አይቀሬ ለሆነዉ ሕዝባዊ አመፅ በሁሉም መስክ መዘጋጀት፤ ጠላትን በሚገባ ማወቅና በሁሉም መስክ ጠላትን ማወከብ የታጋይ ድርጅቶች ሁሉ ሃላፊነት እንደሆነ አስገንዘበዋል። እንዲሁም የሃገራችንን ዉስብስብ ችግር ለመፍታት የሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች፡ ሰብሰቦችና ለሃገሩ የሚቆረቆር ዜጋ ሁሉ የተባበረ ጥረት

እንደሚጠይቅና ባንድ ድርጅት ወይም ስብስብ ብቻ ችግሮች ሁሉ እንደማይፈቱና ለሃገራችን የምንመኘዉን ለዉጥ ማምጣት እንደማይቻል አስገንዝበዋል። ለዚህ ም ተባብሮ መስራት እንደሚያስፈልገና ትብብሩም በተግባር የሚታይ በዚያዉ በዋናዉ በትግሉ መስክ በሃገር ዉስጥ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል።

አያይዘውም ኢሕአፓ በአሁኑ ወቅት ከመቼዉም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ሕዝቡን በማደራጀትና በመቀስቀስ ላይ እንደሚገኝ ፤ በስፋትም በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆነና በተለይ የትግሉ ዋና መድረክ በሆነዉ በሀገራችን ዉስጥና የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነዉን ሕዝብና በተለይም ወጣቱን ማደራጀት አይነተኛ ተግባሩ በማድረግና በመሆኑ፤ ኢሕአፓ ተተኪዉን ትዉልድ በማደራጀትና ኢወክንድን በመመስረት፤ ወጣቱን በዉጭም ሆነ በዉስጥ በማሰባሰብና ለትግሉ በማዘጋጀት፤ በተጠናከረና በስፋት እየሰራ እንደሆነ አስረድተዋል።

በመጨረሻም፤ ኢሕአፓ የሚያካሂደዉን ትግል ለመደገፍና ለማበረታታት ጊዜአቸዉን ሰዉተዉ በዉይይቱ የተሳተፉትን ወገኞች በራሳቸዉና በድርጅታቸዉ ስም ከፍተኛ ምስጋና በማቅረብና የዚህ አይነቱ መቀራረብና መወያየት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዉ ፤ ወቅቱ ትግል የሚፋፋምበት ጊዜ መሆኑን በማስገንዘብ ፤ ኢሕአፓ ዛሬም በፅንዓት ቆሞ ታግሎ በማታገል ላይ ስለሚገኝ፤ እርዱኝ፤ ደግፉኝ፤ እንተባበር ይላል ብለዋል።

ከአቶ ፋሲካ በለጠ ሰፊና ትምህርታዊ ገለፃ በዉሓላ ፡ቤቱ በወቅታዊና አካባቢያዊ አጀንዳወች ላይ ሰፊ ዉይይትና ምክክር አካሂዷል። ሕዝባዊ ትግሉን ለማጠናከርና ለድል እንዲበቃ ለማድረግ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ ወስዶበታል። ተሰብሳቢው አንዳንድ ዉሳኔዎችንም ወሰኖ፤ የዚህ አይነት ግልፅና ትምህርታዊ ዉይይት ለወደፊቱ እንዲቀጥል በመስማማት፡ የዘረኛዉን የወያኔን አምባ ገነንና ከፋፋይ ስርአት ከስሩ ፈንግሎ ለመጣል ተባብረን መስራት በምንችልባቸዉ ሥራወች ሁሉ ባካባቢያችን ለመተባበር ተስማምተናል፡

በመጨረሻም ኢሕአፓ የሚያካሂደዉን እልህ አስጨራሽ ሁለገብ ትግል በመደገፍና በማበረታታት ከጎናችን የቆሙትን አገር ወዳድና የስብሰባዉን ተካፋይ ኢትዮጵያዊያንን ፤ የስብሰባዉ አዘጋጆች ከልብ በማመስገን ስብሰባዉ ሞራል በሚገነባ ስሜት ተጠናቋል።

ኢትዮጵያ በልጆቿ የተባበረ ትግል

ከዘረኛዉና ከፋፋዩ የወያኔ ስርዓት ነጻ ትወጣለች